በዚሁ ደንብም ላይ አንቀፅ 15 ቁጥር 1 እና 2 ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩ ተወዳዳሪ ወይም ወኪል፣ በማንኛውም ጊዜ ለቦርዱም ሆነ ለሕዝብ የሚያቀርበው መረጃ፣ የሚሠጣቸው መግለጫዎች በእውነት ላይ የተመሠረቱ መሆን እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ የሚያቀርባቸው አቤቱታ ወይም ቅሬታ በተጨባጭ ማስረጃ መደገፍ እንዳለበትም ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም ኢዴአፓ-መድህን መጋቢት 3 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀትር በኋላ እንዲተላለፍለት ያቀረበው የቅስቀሳ ፅሁፍ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የምርጫ ሕግና ደንብ ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ማስተላለፍ የማንችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገ/አምላክ ተካ
የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት
የሬዲዮ ዘርፍ የምርጫ ዴስክ ሰብሳቢ

ግልባጭ፣

- ለብሮድካስት ባለሥልጣን
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ፣
- ለኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስኪያጅ
- ለሬዲዮ ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ
- ለሬዲዮ ዘርፍ ምርጫ ዴስክ
  ኢ.ሬ.ቴ.ድ